# የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ፕሮግራም

## I. መግቢያ

የኢትዮጵያ ወጣቶች ለዘመናት በአገራችን ተንሰራፍቶ የቆየውን የጭቆና አገዛዝ ለመገርሰስ በተካሄደው ትግል ግንባር ቀደም ሚና እንደተጫወቱ ታሪክ ሁሌም ሲያስታውሰው የሚኖር ሃቅ ነው፡፡

በንጉሳዊው አገዛዝም ሆነ በአምባገነኑ የደርግ መንግስት የኢትዮጵያ ወጣቶች የስርአት ለውጥ ሃሳብ አመንጭዎች በመሆን ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል፡፡ ወጣቶች በተበተነ አኳኋን ይካሄዱ ከነበሩ የትግል እንቅስቃሴዎች ወደተደራጀ የህዝብ ትግል ለመሸጋገር በተካሄደው ታላቅ ተጋድሎም ግንባር ቀደም ተዋናዮች ነበሩ፡፡ ግፈኛውን የደርግ መንግስት አገዛዝ በትጥቅ ትግል ለመገርሰስ በተካሄደው ትግል በከተማም በገጠርም ወጣቶች የብሄርና ሃይማኖት፣ የፆታና የእድሜ ልዩነት ሳይገድባቸው ተፋልመዋል፡፡ በከፈሉት አኩሪ መስዋእት የአምባገነንነትን ስርአት ገርስሰው ለዛሬው የብርሃን ዘመን አብቅተውናል፡፡

የዛሬው ወጣት በታላላቆቹ አኩሪ መስዋእት ፀረ ዴሞክራሲያዊው አገዛዝ ከተገረሰሰ በኋላ በተፈጠረለት አመቺ ዴሞክራሲያዊና የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ እድል በመጠቀም በድህነትና በኋላቀርነት ላይ ክንዱን አንስቷል፡፡ ወጣቱ ትውልድ ለብልፅግናና ለዴሞክራሲ የሚያካሄደው ትግል እስካሁን የተጐናፀፍናቸውን ድሎች አስጠብቆና በአዳዲስ ድሎች አጐልብቶ ከፍተኛ ግባችን ላይ እስክንደርስ መቀጠል ያለበት ሲሆን ትግሉ ስኬታማ ይሆን ዘንድ በአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ መስመር መመራት እንዳለበት ታምኖ በስድስተኛው የኢህአዴግ ድርጅታዊ ጉባኤ ላይ በተላለፈው ውሳኔ መሰረት የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ እንዲመሰረት ተደረ[1]ል፡፡ ሊጉም በዋናነት ሚታገልልት ኣላማ የእናት ፓርቲው የፖለቲካ ፕሮገራም እንዲሳካ ማድረግ ሲሆን በዚህ ላይ በመመስረት የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ፕሮግራም ተቀርጻል፡፡

በዚህ መሰረት ቀደምት ታጋዮች በተሳካ ሁኔታ በማካሄድ ላይ ያሉትን የለውጥ ጉዞ ተረክቦና ፈሩን አስጠብቆ በከፍተኛ የሃላፊነት መንፈስ ለማስቀጠል ይቻል ዘንድ ትግሉ በየዘመኑ ወጣት ትውልድ መቀጠል እንዳለበት በማመን የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ተደራጅቷል፡፡ ሊጉ ቀጥለው የተዘረዘሩትን ጉዳዮች ታሳቢ በማድረግ የሚታገልለትን ፕሮግራም የቀረፀ ሲሆን የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ በዚህ ፕሮግራም የሚያምኑና ለተግባራዊነቱ ፀንተው የሚታገሉ ወጣቶችን በማሰባሰብ የተደራጀና

በአገራችን የተጀመረው የለውጥ ጉዞ ተጠናክሮ እንዲቀጥል የበኩሉን ሚና የሚጫወት አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ የኢህአዴግ ክንፍ የወጣቶች አደረጃጀት ነው፡፡

## II. የኢህአዴግ ወጣት ሊግን የመመስረት አስፈላጊነት እና መርሆዎች፣

1. በአገራችን ለመጨረሻ ጊዜ ስልጣን ላይ የነበረው አምባገነን የደርግ መንግስት ከተገረሰሰ በሃላ ዴሞክራሲ፣ ሰላምና ልማት የሰፈነበት ህብረተሰብ ለመገንባት የሚካሄደው ጥረት በተሳካ አቅጣጫ በመፈፀም ላይ መሆኑን በመገንዘብ፣
2. አምባገነናዊው አገዛዝ የኢትዮጵያ ወጣቶች ጉልህ አስተዋፅኦ ባደረጉበት ህዝባዊ ትግል ከተወገደ በኋላ በአገራችን ሰላም፣ ዴሞክራሲና ፍትህ የሰፈነበት ዴሞክራሲያዊ የነፃ ገበያ ስርአት ለመገንባት የሚካሄደውን ትግል አስፈላጊነትና በመስኩም ከፍተኛ ደሎች መመዘገበ መጀመራቸውን በመቀበል፣
3. ከአምባገነኑ አገዛዝ መወገድ በኋላ በአገራችን የብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች የእኩልነትና የዜግነት መብቶች ተከብረው ህገ መንግስታዊ እውቅና ያገኙበት ዴሞክራሲያዊ ስርአት መገንባት መጀመሩንና መላ የአገራችን ህዝቦች በአገራቸወና በአካባቢያቸው ጉዳዮች ዋነኞቹ ተዋናዮችና ወሳኝ ሃይሎች መሆን መጀመራቸውን በመቀበል፣
4. በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ዛሬም ዋነኛ ጠላቶቻችን ድህነትና ኋላቀርነት እንደመሆናቸው ሁሉ በሚካሄደው ልማታዊና ስርአት ግንባታ ወጣተቱ ተሳታፊና ተጠቃሚ መሆኑን በማመን፣
5. ኢህአዴግ የነደፋቸው ፖሊሲዎች፣ ስትራተጅዎችና በየወቅቱም የሚነድፋቸው ስልቶች የአገራችንን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ችግሮች የመፍታት ብቃት ያላቸው በመሆኑ በራሱ በኢህአዴግ መሪነት በፅናት ተግባራዊ መሆን እንዳለባቸው በመቀበልና በዚህም ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ ተግባር ወጣት አብዮታዊ ዴሞክራቶች በተደራጀ አኳኋን መሳተፋቸው ለድል አድራጊነታቸው ዋስትና መሆኑን በመገንዘብ፣

6. ወጣቱ ትውልድ በአገራችን ተንሰራፍተው ከቆዩት ድህነትና ኋላቀርነት ዋናው ተጐጅ እንደሆነው ሁሉ በሚካሄደው የልማታዊና ዴሞክራሲያዊ የነፃ ገበያ ስርአት ግንባታ ዋናው ተጠቃሚ መሆን እንዳለበት በማመን፣
7. እስካሁን ድረስ በተካሄዱት ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ ርብርቦች ወጣቱን ለማሳተፍና ለመጥቀም የተደረጉ ጥረቶች እንደተጠበቁ ሆኖ ጥረቶቹ ከወጣቱ ተጨባጭ ችግሮችና ፍላጐት ጋር የሚመጣጠኑ ባለመሆናቸው የወጣቱ ተሳትፎና የተጠቃሚነት ደረጃ ዝቅተኛ ሆኖ መቆየቱንና ይህን የማስወገድን አስፈላጊነት በመገንዘብ፣
8. ወጣቱ ትውልድ በልማታዊና ዴሞክራሲያዊ የነፃ ገበያ ስርአት ግንባታ ተሳታፊና ተጠቃሚ ሊሆን የሚችለው ከማንም በላይ ራሱን አደራጅቶ በተነሳሽነት በሂደቱ ሲሳተፍ ብቻ መሆኑን በመገንዘብ፣
9. ወጣቶች በአገር ግንባታ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚካሄደው ጥረት ሊሰምር የሚችለው በወጣቱ የተደራጀ ተሳትፎና እንቅስቃሴ ላይ የሚታዩ አላግባብ የመጠቀም ስሜቶች ተወግደው ወጣቱ በልማታዊና ዴሞክራሲያዊ አቅጣጫ ተሳታፊና ተጠቃሚ ሊሆን ሲችልና ይህም ለወጣቱ ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ ጉዞ መጠናከር የቆሙ የወጣት አብዮታዊ ዴሞክራቶች ፖለቲካዊ ድርጅት ወይም ሊግ በመመስረት ሊሳካ እንደሚችል በመቀበል፣
10. የኢትዮጵያ ወጣቶች ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ይጐለብት ዘንድ መንግስት ቀደም ሲል የወጣቶች ፖሊሲ በኋላም ደግሞ የወጣቶች ፓኬጅ አዘጋጅቶ በራሱ በወጣቱ ባለቤትነትና የተደራጀ ተሳትፎ ተግባራዊ የሚሆንበትን ሁኔታ ማመቻቸቱ የወጣቱን ትግልና ተጠቃሚነት ለማጠናከር ልዩ ሚና የሚጫወት እንደሆነ በመገንዘብ፣
11. የአገራችን/ክልላችን ወጣቶች በአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ የወጣቶች ሊግ ብቻ ሳይሆን ንቃታቸው በፈቀደላቸውና ጥቅማቸውንና ተሳትፏቸውን ለማረጋገጥ ያመቻናል በሚሉት የአደረጃጀት መልክ ተሰባስበው መታገላቸውን በመቀበልና ይህም እንዲጠናከር አቅሙ የፈቀደውን ሁሉ ማድረግ እንዳለበት በማመን፣
12. የአገራችን ወጣቶች በተለያዩ አጀንዳዎችና የአደረጃጀት መልኮች ዙሪያ ተሰባስበው የሚያካሂዱት ትግል ተገቢ በመሆኑ የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ድጋፍ የማይለየው ቢሆንም ትግሉ ለወጣቱ የላቀ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ዋስትና ሊሆን የሚችለው በበርካታ የአደረጃጀት መልኮች ተበታትኖ ከመታገል በተጨማሪ

በአንድ የጋራ ድርጅታዊ ጥላ ስር ተሰባስቦ በመታገል ጭምር እንደሆነ በመቀበል፣

13. ለዚህም ሲባል የተለያዩ የኢትዮጵያ ወጣቶች አደረጃጀቶች በሂደት አንድ አገራዊ/ክልላዊ የወጣቶች ማህበራት ፌዴሬሽን መመስረት እንደሚያስፈልጋቸውና የወጣቶች ማህበራት ፌዴሬሽን ሊጉን ጨምሮ ሁሉንም የወጣት ማህበራት የሚያሰባስብ እንዲሆንና በወጣት ማህበራቱ መካከል የሚኖረው ግንኙነትም በእኩልነት ላይ የተመሰረተ ዴሞክራሲያዊ ግንኙነት ሊሆን እንደሚገባው በመቀበል፣
14. የአገራችን ወጣቶች በአጠቃላይ በልማታዊና ዴሞክራሲያዊ መስመር እየተመሩ በተጀመረው የለውጥና የአገር ግንባታ ሂደት በተደራጀ አኳኋን የሚያደርጉት ተሳትፎ በትክክለኛ መርሆዎችና አቅጣጫዎች እስከተመራ ድረስ ቀጣዩን የአመራር ትውልድ ለመፍጠር ልዩ ሚና እንደሚጫወት በመቀበል፣
15. በአገራችን ድህነትንና ኋላቀርነትን ድል አድርጎ ብልፅግና፣ ፍትህና ዴሞክራሲን የዳበረ ደረጃ ላይ ለማድረስ የሚካሄደው ትግል ሊሳካ የሚችለው ትግሉ በአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብና ድርጅት ሲመራ እንደሆነ በመገንዘብ፣
16. በአገራችን በመካሄድ ላይ ያለው ለውጥ በኢህአዴግ ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ መሪነት እያስመዘገበ ያለውን ከፍተኛና ፈጣን የእድገት ምጣኔ ለማስቀጠል የሚቻለው የኢህአዴግን አመራር ተቀብሎ ለልማታዊና ዴሞክራሲያዊ መስመሮቹ በፅናት በመረባረብ እንደሆነ በማመን፣
17. ኢህአዴግ አምባገነናዊውን አገዛዝ ለማስወገድና ከዚያም በኋላ ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ለመገንባት በሚያካሄደው ህዝባዊ ትግል በመሰረቱ ብቁና ትክክለኛ አመራር እንደሰጠና መስጠትም እንደሚቀጥል በማመን፣
18. በኢህአዴግ ፕሮግራም የተዘረዘሩትን ግቦች ማሳካት ከድህነትና ኋላቀርነት የተላቀቀች፣ መካከለኛ ገቢ ያላትን ኢትዮጵያን ለመፍጠር ወሳኙ ጉዳይ እንደሆነ እና ከኢህአዴግ ጥላስር መሰባሳብ በማመን።

## III. የኢህአዴግ የወጣቶች ሊግ የፖለቲካ መርሃ ግብር

### የኢህአዴግ የወጣቶች ሊግ የፖለቲካ ዓላማ

ወጣቱ ህገ-መንግስቱ ያረጋገጠለትን ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች በተገቢው በመገንዘብ በተሟላ መልኩ እንዲከበሩለት እና በአገሪቱ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የነቃ እና ዲሞክራሲያዊ ተሳትፎውን እንዲያጎለብት ከዚህ ባሻገርም በእኩልነትና በመፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ የኢትዮጵያ ህዝቦች ጠንካራ አንድነት እንዲጎለብትና የዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታው አካል መሆን ነው:: ይህን ስትራቴጂያዊ የፖለቲካ ዓላማ ለማሳካትም የሚከተለውን የፖለቲካ መርሃ ግብር ተግባራዊ ያደርጋል::

1. ህገ-መንግስታዊ ዋስትና ባገኙት የዴሞክራሲ መብቶች ወጣቶች ዋነኛ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ
   1.1. በህገ-መንግስቱ እውን የሆኑት ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለወጣቱ ብሎም ለሁሉም ዜጎች በተሟሏ አኳኋን ተከብረው እንዲቀጥሉና ይበልጥ እየዳበሩ እንዲሄዱ መታገል::
   1.2. የሁሉም ዜጎች መብቶች በሚከበርበት የዴሞክራሲ ስርዓት ውስጥ ሰፊው ወጣት በነዚህ መብቶች በሰፊውና በተሟላ ሁኔታ እንዲጠቀም መታገል::
   1.3. ወጣቱ ህገ-መንግስቱ ያረጋገጠለትን ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች እንዲጠበቁለትና በስራ እንዲተረጎሙ መታገል በተለይም የዜጎችን ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ መታገል::
   1.4. ለዲሞክራሲ ማበብ ተፈላጊ ከሆኑ አደረጃጀቶች ውስጥ አንዱ የብዙሃን ማህበራት አደረጃጀት በመሆኑ እነዚህ የሰፊው ወጣት አደረጃጀቶች ነፃነታቸው ተጠብቆ ህጉን ተከትለው እንዲስፋፉና እንዲጠናከሩ መታገል::
   1.5. በወጣቱ መካከል የመቻቻልና ልዩነቶችን በዲሞክራሲያዊ ባህል የመፍታት ሁኔታ እንዲዳብርና ለጋራ አገራዊ ጥቅም እንዲቆሙ መስራት::
   1.6. እነዚህን መብቶች ለማፈን፣ ለመሸራረፍ፣ የዴሞክራሲ ስርዓቱን ለመናድና ለመቀየር የሚደረግን ማንኛውም ህገ-ወጥ ተግባር በጥብቅ መታገል::
2. እየተገነባ ባለው ዴሞክራሲያዊ ስርዓት የሰፊውን ወጣት ነፃና ዲሞክራሲያዊ ተሳትፎ ማረጋገጥ
   2.1. ወጣቱ በመንግስትም ሆነ በህብረተሰቡ ተገቢውን ትኩረት እንዲያገኝ መታገል

2.2. ወጣቶች ነፃና ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ሃሳባቸውን የሚገልፁበት በእቅድ ዝግጅትና አፈፃፀም የሚሳተፉባቸው መድረኮች እንዲፈጠሩ መስራትና በተፈጠሩ ምቹ ሁኔታዎች በተደራጀ መልኩ መጠቀም።

2.3. ወጣቶችን በአጠቃላይ በህብረተሰብ ጉዳዮች በተለይ ደግሞ በራሳቸው ጉዳዮች በሰፊውና በተደራጀ አኳኋን ለማሳተፍ የሚያስችል ስርዓት እንዲፈጠርና እንዲጠናከር መታገል።

2.4. ወጣቶች በርካታ ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጥያቄዎች ያሏቸው በመሆኑ በራሳቸው ጉዳይ ላይ ከማንም በፊት ተቆርቋሪ፣ ተጎጂና ተጠቃሚ የሚሆኑት እነርሱ በመሆናቸው ዋነኛ ችግር ፈቺነታቸውን በተግባር ለማረጋገጥ የሚያስችሉ የተሳትፎ መድረኮች እንዲመቻቹለት ተግቶ መስራትና የተከፈቱ መድረኮች በአግባቡ መጠቀም።

2.5. ወጣቱ ዋነኛ ችግር ፈቺ ሃይልነቱን እንዳይገነዘብ የሚያደርጉ አዝማሚያዎችን በቀጣይነት በመታገል የማስተካከልና የወጣቱን በራስ የመተማመን አቋም ማጠናከር።

2.6. ወጣቱ መድረክ እንዳይኖረው ወይም በተከፈቱ መድረኮች በብቃት እንዳይጠቀም የሚያደርጉ ዝንባሌዎችን እየለዩ በማያቋርጥ ሁኔታ በራሱ በወጣቱ ወሳኝ ተሳትፎ እንዲፈታ ማድረግ።

2.7. ወጣቱ በየስራ መስኩና በየፍላጎቱ ዙሪያ እንዲደራጅና ለወጣቱ የጋራ ጥያቄዎች የጋራ አደረጃጀቶች እንዲጎለብቱ ማድረግ እና ወጣቱ በነዚህ አደረጃጀቶች መብትና ጥቅሙን እንዲያስከብር፤ ዴሞክራሲያዊ አሰራራቸው የተጠበቀ እንዲሆን መታገል።

2.8. የተለያዩ የወጣት አደረጃጀቶች የወጣቱን የጋራ ጥያቄዎች ከግብ ለማድረስ በፌደሬሽን እና ኮንፌደሬሽን የወጣት አደረጃጀቶች እንዲደራጁ፣ አደረጃጀቶቹም በመካከላቸው ዲሞክራሲያዊና በዕኩልነት ላይ የተመሰረተ ግንኙነት እንዲኖራቸው መታገል።

2.9. ወጣቱ በተግባር ነጥሮ እንዲወጣ፣ የአመራር አቅሙ በየደረጃውና በየመድረኮቹ በሚኖሩት ተሳትፎዎች ይበልጡኑ እንዲጎለብት በማድረግ አቅሙ እንዲገነባና የበኩሉን ሚና እንዲጫወት የአመራር አቅሙን የሚገነባባቸው ሂደቶችን የሚያደናቅፍ ችግሮችን እየተከታተሉ እነዲፈታ መታገል።

3. ወጣቶች በህዝቦች መብት መከበር፣ በእኩልነትና በመፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ ጠንካራ ዴሞክራሲያዊ አንድነት እንዲፈጠር መታገል፡፡

3.1. በህገ- መንግስቱ የተረጋገጠ የብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች የራስን ዕድል በራስ መወሰን እስከ መገንጠል ያላቸው መብት እንዳይሸራረፍ መታገል፡፡

3.2. ህዝቦች ህገ-መንግስታዊ መብታቸው በተከበረበት ሁኔታ ለነፃ ፍላጎታቸውና በመፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ አንድነት እንዲኖራቸው ያለማሰለስ መታገል፡፡

3.3. የሁሉም የኢትዮÉያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ታሪክ እንዲታወቅ፣ ባህላቸው እንዲጎለብትና እንዲከበር መስራት፡፡

3.4. በህዝቦች እኩልነት መከባበርና መፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ ዴሞክራስያዊ አንድነትና አመለካከት በወጣቱ ውስጥ እንዲሰርፅ ያላሰለሰ ትግል ማካሄድ፡፡

3.5. የህዝቦችን ዴሞክራሲያዊ አንድነት የሚሸረሽሩ የጠባብነትና የትምክህተኝነትን አመለካከቶችን ያለማቋረጥ መታገል አነዚህ አስተሳሰቦች ከህዝቡ በአጠቃላይ ከወጣቱ በተለይ እንዲወገዱ መታገል፡፡

3.6 በየደረጃው የሚታዩ የመልካም አስተዳደር ጉድለቶች እና የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ድርጊት ከህብረተሰቡ ጋር በመሆን እንዲስተካከሉ መታገል፡፡

3.7. ወጣቱ ትውልድ የሀገራችን ብሄሮች፣ብሄረሰኖችና ህዝቦች የጋራ እሴቶች የሆኑትን የህዝባችንን ባህል፣ ታሪክ፣ k3k ወዘተ ማወቅ፣ መንከባከብ ፣ እንዲታወቁና እንዲስፋፉ ማድረግ እንዲሁም ኃላቀርና ጎጂ ድርጊቶች እንዲወገዱ መታገል፡፡

3.8 ወጣቱ ዕርስ በዕርሱ የሚገናኝበት፣ የሚተዋወቅበትና ለጋራ ጥቅምና መብቶቹ መከበረ በጋራ የሚታገልባቸው መድረኮች እንዲስፋፉና እንዲጠናከሩ መታገል፡፡

## IV የኢኮኖሚ መርሃ ግብር

. የኢህአዴግ የወጣቶች ሊግ የኢኮኖሚ አላማ

በአገራችን ህዝብን በየደረጃው ተጠቃሚ የሚያደርግ ፈጣን ልማትን ዕውን ለማድረግ በኢህአዴግ የተነደፈውን ፖሊሲና ስትራተጂ በመላው የህዝብ ተሳትፎ ተግባራዊ ማድረግ፡፡ እንዲሁም ወጣቱ በኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ቁልፍ ተዋናይና በጥረቱ ተጠቃሚ እንዲሆን ማስቻል፡፡

1. ገጠርንና ግብርናን ማዕከል ባደረገው የልማት ስትራቴጂ ውስጥ የወጣቱን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፡፡

አሁን ባለንበት ሁኔታ ያሉን ዋነኛ ሃብቶቻችን መሬትና ሰፊ የህዝብ ጉልበት ነው፡፡ እነዚህን ያሉንን ሃብቶች መሰረት በማድረግ ወጣቱ ያለውን እምቅ ጉልበትና እውቀት መነሻ አድርጎ በኢኮኖሚው አቅሙ እንዲጠናከር በተለይም የገጠሩ ወጣት ኢኮኖሚያዊ ጥያቄ በተገቢው እንዲመለስ መታገል፡፡

1.1. ወጣቱ በቤተሰቦቹ መሬት ላይ በሚካሄደው ልማት ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆን ለማድረግ ተገቢውን ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ መስራት፡፡

1.2. በቤተሰብ መሬት ላይ የሚካሄደውን ልማት ለስራ የደረሱ የቤተሰቡን አባላት ጉልበትና የሚቀርቡ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች አሟጦ በመጠቀም ተጨማሪ ምርት በማምጣት ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ማድረግ ወጣቶች በዚህ ረገድ ከፍተኛ ሃላፊነት እንዳለባቸው እንዲገነዘቡ መስራት፡፡

1.3. በየቀበሌው ሊታረሱ የሚችሉና በግል ያልተያዙ የእርሻ መሬቶች በፍትሃዊ መንገድ ለወጣቱ እንዲከፋፈሉ መታገል፡፡

1.4. ወጣቶች ባገኙት መሬት ላይ ከፍተኛ ዋጋ የሚያወጡ ገበያ ተኮር ምርቶችን አምርተው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተገቢውን ድጋፍ የሚያገኙበትን ስልት እንዲቀየስ መታገል፡፡

1.5. ተራሮች ለወጣቱ እንዲከፋፈሉና ወጠቶች አልምተው እንዲጠቀሙ የስልጠና የማቴሪያል አቅርቦትና የብድር አገልግሎት የሚያገኙበትን መንገድ እንዲመቻች መታገል፡፡

1.6. ሰፊ እና ለኑሮ ምቹ በሆነ አካባቢዎች ወጣቶች በሰፈራ ፕሮግራም ታቅፈው እንዲሰፍሩ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮቻቸውን በመፍታት እራሳቸውን እንዲችሉ ለማድረግ ለዚህም ተገቢውን ድጋፍ እንዲያገኙ መታገል፡፡

1.7. ከግብርና ውጭ ላሉ የገጠር ልማት ስራዎች ማለትም በጥቃቅን የንግድ ስራዎች፣ በገጠር ባሉ የኮንስትራክሽን ስራዎች እንዲሁም በከተሞች በፍጥነት በማደግ ላይ ላለው የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ የሚሆን ጥሬ ዕቃ የማቅረብ እንቅስቃሴ በተደራጀ መልኩ እንዲሳተፉና ልዩ ልዩ የዕደ ጥበብ ስራዎችን በማስፋፋት ተጠቃሚ እንዲሆኑ መታገል፡፡

1.8. ወጣቱ ከተረጂነትና ጠባቂነት አመለካከት ተላቆ የራሱን ችግር በራሱ ጥረት ለመፍታት እንዲችል መታገል፡፡

1.9. ወጠቱ የብድር አገልግሎት እንዲያገኝና የቁጠባ ባህል እንዲያዳብር መስራት::

1.10. የአርብቶ አደር ወጣቶች በአገሪቱ የልማትና የዴሞክራሲ ግምባታ ጉሉህ ሚና እንዲጫወቱና ተጠቃሚ እንዲሆኑ መታገል::

**2. በከተማ እና ኢንዳስትሪ ልማት ስትራቴጂ ውስጥ የወጣቱን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ**

2.1 በከተማ የሚገኙ ወጣቶች በከተሞች በሚካሄደው ልማት ንቁ ተዋናይና ተጠቃሚ እንዲሆኑ መታገል::

2.2 በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ውስጥ የሚሰማሩ ወጣቶች የሙያ ችሎታ እንዲዳብርና ተጠቃሚነታቸውም ይበልጥ እንዲጨምር ስልጠናዎችን እንዲያገኙ መታገል::

2.3 ወጣቶች በተከሞች በሚካሄዱ ልዩ ልዩ የአነስተኛና ጥቃቅን የልማት ተቋማት ፈጠራዎችና የማስፋፋት ስራዎች ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ መስራት::

2.4 ወጣቶች የከተማ ግብርናን በማስፋፋት ሂደት ላቅ ያለ ሚና እንዲኖራቸው ማበረታታት::

2.5 ወጣቶች ስራ ፈጣሪ እንጂ ስራ ጠባቂ እንዳይሆኑ በአመለካከት ረገድም ለስራ የሚሰጡትን ዝቅተኛ ግምት እንዲያስወግዱና የአመለካከት ለውጥ እንዲያመጡ መስራት::

2.6. ወጣቶች በልዩ ልዩ ማህበራት እንዲደራጁና ለምርታቸው ገበያ እንዲፈጥሩ ለማስቻል መስራትና ማበረታት::

## V. ማህበራዊ መርሃ ግብር

**የኢህአዴግ የወጣቶች ሊግ ማህበራዊ አላማ**

በየደረጃው የተሟላ ማህበራዊ ለውጥ እንዲመጣ የወጣቱን ማህበራዊ ችግሮች ለመፍታት በሚያስችሉ ፖሊሲና ስትራቴጂዎች ተግባራዊነት ወጣቱ በራሱ ዋነኛ ሃይልና ንቁ ተሳታፊ በመሆን ተጠቃሚ እንዲሆን መታገል::

**1. ትምህርት**

ወጣቱ ለላቀ የትምህርትና ስልጠና እድል እንዲበቃ መስራት ::

በትምህርት ገበታ ላይ ያሉ ወጣቶች ጥራቱ የተጠበቀ ትምህርት እንዲያገኙና ትምህርትን በማስፋፋት ሂደቱ የሚታዩ ችግሮችን ለመቅረፍ በሚካሄደው ጥረት

ላይ ንቁ ተዋናዮች እንዲሆኑ በትምህርት ጥራትና በትምህርት ተቋማት ማሻሻያ ፕሮግራም ውስጥ የበኩላቸውን ሚና እንዲጫወቱ ማድረግ::

ወጣቶች በስነ- ምግባርና ስነ ዜጋ እሴቶች ታንፀው ለስራ ብቁ የሚሆኑበትን አመለካከት እንዲያዳብሩ አካላዊና አእምሮአዊ ግንባታን በማጠናከር መስራት::

ያልተማሩ ወጣቶች ከመሰረተ ትምህርት ጎን ለጎን እንዲሁም በተለያዩ ምክንያቶች ትምህርታቸውን ያቋረጡ ወጣቶች ፍላጎታቸውን መሰረት ያደረገ የሞያ/የክህሎት ስልጠና እንዲያገኙ መስራት::

በከተሞች የት/ት ዕድል ያላገኙና አቋርጠው ለስራ አጥነት የተዳረጉ ወጣቶች የሙያ/የክህሎት ስልጠና እንዲያገኙ መስራት::

1.6. ትምህርት ቤቶች የትምህርትና ስልጠና ቁሳቁሶችን ለወጣተ ወንዶችና ለወጣት ሴቶች መሟላት ያለባቸውነ አገልግሎቶች እንዲያሟሉ መታገል::

1.7. የትምህርት እድል ያላገኙ ወጣቶች የትምህርት እድል እንዲመቻችና በችግር ምክንያት ያቋረጡት ትምህርታቸውን እንዲቀጥሉ መታገል::

1.8. ወጣቱ ዘመኑ ከሚፈቅደው ቴክኖሎጂ ጋር እንዲራመድ የሙያና ቴክኒክ ስልጠናዎችን ዕድል የሚያገኙበትን ሁኔታ እንዲመቻች መታገል::

## 2. ጤና

2.1 ወጣቱ በሽታን የመከላከል ግንዛቤውን በማሳደግ ለበሽታ ያለውን ተጋላጭነት ለመቀነስ፣ በመከላከልና በመሰረተ ጤና ላይ ያተኮረ የነቃ ተሳትፎ እንዲያደርግ ለማድረግ፤ በተለይም የግል ንፅናና የአካባቢ ንፅህናን የመጠበቅ የአመጋገብ ስርአት በማስተካከል ዙሪያ የባህል ለውጥ ለማምጣትመታገል::

2.2 ወጣቱ ኤች አይቪ ኤድስ፣ ወባና ሌሎች ተዛማጅ በሽታዎች የሚስፋፉበትን መንገድ እንዲገነዘብና መከላከያ መንገዶችንም አውቆ የአስተሳሰብ ለውጥ እንዲያመጣ መስራት::

2.3. በበሽታ የተጎዱ ወገኖቹን መንከባከብ እንዲያስችለው ማህበራዊ ሁኔታዎችን ማመቻቸት::

2.4 ወጣቱ ኤች አይቪ ኤድስና ተላላፊ በሽታዎችን ነፃ የምርመራ አገልግሎት የሚያገኝበት ሁኔታ እንዲስፋፋ መስራት::

2.5 ወጣቱ በስነ-ተዋልዶ ጤና ላይ ያለው ግንዛቤ እንዲያድግና የተሟላ መረጃ በማግኘት የሚጠበቅበትን አውቆ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርግ መታገል::

## 3. ሌሎች ማህበራዊ ጉዳዮች

3.1 በወጣቱ ፍላጎትና ተሳትፎ ላይ የተመሰረቱ የመዝናኛ አገልግሎቶችና የወጣቶች መዋያ እንዲስፋፉ መታገል፡፡

3.2. በየደረጃው የሚገኙ ወጣቶች የንባብ ባህላቸውን ለማሳደግ እንዲያስችል የቤተ መፅሃፍት አገልግሎት እንዲስፋፉ መታገል፡፡

3.3. በየደረጃው የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ከተሟላ አገልግሎት ጋር ለወጣቱ እንዲቀርብ ወጣቱ፣ ህብረተሰቡ፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ርብርብ እንዲያደርጉ መስራት፡፡

3.4. ወጣቶች በልዩ ልዩ ባህላዊና ዘመናዊ ስፖርት ውድድሮችና ፌስቲቫሎች የሚሳተፉበትና ጠንካራ አንድነትና ጤናማ የውድድር መንፈስ የሚያዳብሩበት ሁኔታ እንዲኖር መታገል፡፡

3.5. ወጣቱ በተለያዩ ክልላዊና አገራዊ በዓላት ንቁ ተሳታፊ የሚሆንበትን እንዲሁም የዕራሱ የሆነ የወጣቶች ቀን እንዲኖር እና በልዩ ልዩ እንቅስቃሴዎች የሚያከብርበት ሁኔታ እንዲፈጠር መታገል፡፡

3.6 የተለያዩ መገናኛ ብዙሃን ለወጣቱ ትኩረት ሰጥተው ትምህርታዊና አዝናኝ ፕሮግራሞችን በወጣቱ ተሳትፎ እንዲያቀርቡ መስራት፡፡

3.7. በወቅታዊ ሃገራዊና ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎች ላይ የሚመክርበትና የተማላ ግንዛቤ የሚፈጥርበት የተለያዩ መድረኮች እንዲኖሩ መስራት፡፡

3.8. ወጣቶች ለህብረተሰቡ ነፃ ማህበራዊ አገልግሎቶችን የመስጠት ባህል እንዲያዳብሩ በተለያዩ የማህበረሰብ ነፃ አገልግሎቶች እንዲሳተፉ ማድረግ፡፡

3.9. ወጣቶች ኃላቀርና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን በመለየት የማስወገድና ጠቃሚ ባህሎችን በማዳበር እንዲቀጥሉ እና ከትውልድ ትውልድ እንዲተላለፉ መስራት

3.10. አሁን ያለውን ኃላቀርና ያልዳበረ የስራ ባህል፣ አመጋገብና የአኗኗር ባህላችንን ወደ ተሻለ ደረጃ እንዲሸጋገር መታገል፡፡

3.11.ወጣቶች በአካባቢ ጥበቃና እንክብካቤ በመሳተፍ አካባቢያቸውን አረንጓዴ እንዲያለብሱ የተለያዩ መርሃ ግብሮችን ማዘጋጀትና በስራ ላይ ማዋል፡፡

3.12 በወጣቱና ብሎም በህብረተሰቡ የፆታ እኩልነት፣የአካል ጉዳተኞች እኩልነት እንዲረጋገጥ መታገል፡፡

## VI. የውጭ ግንኙነት መርሃ ግብር

### 1. የኢህአዴግ የወጣቶች ሊግ የውጭ ግንኙነት ዓላማ

የኢህአዴግ የወጭ ገንኙነት ምርህግብር መነሻ በማድረግ ከሌሎች ተመሳሳይ አደረጃጀቶች ጋር ምቹ የሆነ የስራ ግንኙነት ለመፍጠር የሚያስችልና ይህንኑ የሚያሳካ የሚከተለውን የውጭ ግንኙነት መርሃ ግብር ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

1.1. በየደረጃው የሚመሰረተው የሊግ አመራር ከኢህአዴግ አመራር ጋር በቅርበት የሚሰራ እና የድርጅቱን ውሳኔዎች የሚያከብር፣ ከሊጉ ጋር በሚጣጣም መልኩ በስራ ላይ የሚያውል እና አጠቃላይ አቅጣጫውን ከፖለቲካ ድርጅቱ የሚያገኝ ይሆናል፡፡

1.2. ሊጉ ከማህበራት ጋር እንደ አደረጃጀት የአቻነትና የመተባበር ግንኙነት የሚኖራቸዋል፡፡

1.4. ሊጉ በየደረጃው ከአሉት ማህበራት ጋር በመተባበር በጋራ ጉዳዮች ዙሪያ የመስራቱ ሁኔታ እንዳለ ሆኖ ከሌሎች ሀገሮች ሊጎች ጋርም በሀገሪቱ የውጪ ፖሊሰ እና የኢህአዴግ የወጭ ገንኙነት መርህ ላይ በመመርኮዝ ግንኙነት የማድረግና ወንድማማችነትን የማጠናከር፣ የመደጋገፍ፣ ልምድ የመለዋወጥ፣ ተግባራትን ሊያከናውን ይችላል፡፡

# የኢህአዴግ ወጣቶች ሊግ ፕሮግራም

**ግንቦት 2001ዓ/ም**